# ፈጣን የምዝገባ መመሪያ

## MCPS Regulation JEA-RB, Enrollment of Students ይመልከቱ፦

ወደ ሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) እንኳን ደህና መጡ። የት/ቤት ምደባ ሊደረግ የሚችለው የተመዝጋቢ ተማሪው(ዋ)ን መደበኛ የመኖሪያ አድራሻን/bona fide residence መሰረት በማድረግ ነው። ልጅዎ የትኛው ት/ቤት መግባት እንዳለበ(ባ)ት ካላወቁ፣ እባክዎ "Division of Capital Planning" በስልክ ቁጥር፦ 240-314-4710 ደውለው ይጠይቁ ወይም ድረ-ገጽ ይጎብኙ፦www.montgomeryschoolsmd.org/departments/planning እና "Find Your School" የሚለውን ጠቅ ያድርጉ።

ሴፕቴምበር 1 ላይ እድሜአቸው 7 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ባለፉት ሁለት ዓመታት በዩ.ኤስ የትምህርት ሥርአት ውስጥ (ወይም በዩ.ኤስ የመከላከያ ዲፓርትመንት ት/ቤቶች ወይም በውጭ አገር ያሉ እውቅና የተሰጣቸው የአሜሪካ ኢንተርናሽናል ት/ቤቶች) ትምህርት ያልተከታተሉ ተማሪዎች የምዝገባ ሂደት ለመጀመር ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ዓለም አቀፍ የምዝገባ እና ምደባ ክፍል - MCPS International Admissions and Enrollment (IAE) መላክ አለባቸው የስልክ ቁጥር፦ 240-740-4500። እድሜአቸው ከ7 ዓመት በታች የሆኑ ተማሪዎች በቀጥታ በአካባቢያቸው ት/ቤቶች ሊመዘገቡ ይችላሉ።

ተማሪዎችን ወደ MCPS (አዲስ ወይም እንደገና) የሚያስገቡ ወላጆች/ሞግዚቶች ሁሉ የሚከተሉትን ማረጋገጫዎች ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፦ የተወለደ(ች)በት ቀን፣ የተማሪ መለያ (ስም)፣ የወላጅ/የአሳዳጊ መለያ እና ከተማሪው/ዋ ጋር የዝምድና/የግንኙነት ማረጋገጫ፣ መኖሪያ፣ የክትባት ማስረጃዎች፣ ቤት አልባ ካልሆኑ በስተቀር፣ MCPS Forms 560-24፣ የአዲስ ተማሪ መረጃ/ኢንፎርሜሽን፣እና MCPS Form 565-1፣ የተማሪ ድንገተኛ/አስቸኳይ ሁኔታ መረጃ/ኢንፎርሜሽን - Student Emergency Information ተሞልቶ መቅረብ አለበት።

እድሜ—5–21
- ሴፕቴምበር 1 ላይ ቢያንስ አምስት ዓመት እድሜ የሚሆናቸው እና በወቅቱ የትምህርት ዓመት የመጀመሪያው ቀን ከ 20 ዓመት እድሜ ያልበለጡ ተማሪዎች የዩ.ኤስ ዜግነት ያላቸውም ይሁኑ ወይም የዩ.ኤስ ዘግነት የሌላቸው ለመመዝገብ ብቃት አላቸው።

ማንነት—ተማሪው(ዋ)ን የሚያስመዘግብ ሰው መገኘት አለበ(ባ)ት
- ህጋዊ መታወቂያ እና
- ከተማሪ ጋር የዝምድና/ግንኙነት ማስረጃ

ነዋሪነት—በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ
- ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ የቤት ባለቤት ከሆኑ፣ ተቀባይነት የሚኖረው ሠነድ የወቅቱ የባለንብረትነት ታክስ መክፈያ ሠነድ ይሆናል። ከሞንትጎሞሪ ካውንቲ የፋይናንስ መምሪያ በ 240-777-0311 (በመደወል) ወይም በ montgomerycountymd.gov/finance ቅጂ ማግኘት ይቻላል፣ ወይም
- ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ተከራይቶ(ታ) የሚኖር/የምትኖር ከሆነ(ች)፣ ተቀባይነት የሚኖረው ሠነድ የወቅቱ የኪራይ/lease ማስረጃ ነው። ዋናው የኪራይ/lease ሠነድ ጊዜው ያለፈበት ከሆነ፣ ወቅታዊ የመብራት/የውኃ/የጋዝ መገልገያ ክፍያ ሠነድ (utility bill) ወይም የኪራይ ጊዜ የተራዘመበት ሠነድ መቅረብ አለበት፣ወይም
- ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ ቋሚ የመኖሪያ አድራሻ በ MCPS ትምህርት ቤት አካባቢ መሆኑ የተረጋገጠ የቤት ባለቤት ጋር ወይም ከተከራይ ጋር በደባልነት በሚኖሩበት አድራሻ ለመመዝገብ የሚፈልጉ ከሆነ የሠነድ ማረጋገጫ የታተመበት/notarized MCPS Form 335-74 የደባልነት መኖሪያ ማረጋገጫ/Shared Housing Disclosure በአግባብ ተሞልቶ መቅረብ አለበት። ቤት ያላቸው፣ ወቅታዊ የንብረት ባለቤትነት ታክስ ክፍያ ሠነድ/property tax bill ተቀባይነት ያለው ሲሆን፣ ለተከራይ፣ የኪራይ ውል/rental lease ተቀባይነት ይኖረዋል። የመጀመሪያው የኪራይ/ሊዝ ሠነድ ወቅቱ ያለፈበት ከሆነ፣ ወቅታዊ የዩቲሊቲ ክፍያ ቢል ወይም የኪራይ/ሊዝ የተራዘመበት ሠነድ መቅረብ አለበት። ወላጅ/ሞግዚት/ብቁ ተማሪ በዚህ አድራሻ ነዋሪዎች መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የቃለመሃላ ጽሑፍ "MCPS Form 335-74" ተፈርሞ፣ የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም ተደርጎበት/notarized እና ሦስት ሠነዶችን ማቅረብ ያስፈልጋል። ተሞልቶ ተፈርሞበት፣ የሠነድ ማረጋገጫ ማህተም ያለበት/notarized የ "MCPS Form 335-74" ስለመኖሪያ አድራሻ ከሚያረጋግጡ ከሦስት ተፈላጊ ማስረጃዎች እንደ አንድ ይቆጠራል።
- ማንኛውም በሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ ያልሆነ(ች) የት/ቤት ክፍያ እየከፈለ(ች) MCPS በተማሪነት ለመመዝገብ ቢፈልግ/ብትፈልግ IAE በስልክ ቁጥር፦ 240-740-4500 መጠየቅ ያስፈልጋል።
- ቤት አልባ ከሆኑ፣ እባክዎን የ Enrollment Information/Homeless Children ድረ-ገጽ ይመልከቱ።

ክትባት—ሁሉም የተሟላ
- የሜሪላንድ የጤና ዲፓርትመንት የክትባት ሠርተፊኬት ቅጽ/Maryland Department of Health (MDH) Immunization Certificate MDH Form 896፣ወይም
- በሃኪም ወይም የጤና ክሊኒክ ኮምፒውተር የተዘጋጀ ቅጽ

# ተቀባይነት የሚኖራቸው የማረጋገጫ/ማስረጃ/ ሠነዶች

## የተማሪ እድሜ እና ማንነት (የልደት እና ስም ማስረጃ)

- የልደት የምስክር ወረቀት
- ፓስፖርት/ቪዛ
- የሃኪም ምስክር ወረቀት
- የጥምቀት ወይም የቤተክርስቲያን የምስክር ወረቀት
- የሆስፒታል የምስክር ወረቀት/ሰርትፊኬት
- የወላጅ በህግ የተመዘገበ ቃለ-መሃላ (የትውልድን ቀን ትክክለኛነት በማረጋገጥ በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ ቃል)
- የልደት ቀን ሠርተፊኬት/ምዝገባ
- ሌላ ህጋዊ ወይም በህጋዊ ቃል ተቀባይ የተመሰከረ የማንነት ማረጋገጫ

## ተማሪን ወደ ት/ቤት የሚያስገባ(የምታስገባ) ወላጅ/ሞግዚት መለያ እና ከተማሪው(ዋ) ጋር ያለው/ያላት ግንኙነት-ዝምድና (የአሳዳጊነት/የሞግዚትነት ማረጋገጫ)

ፎተግራፍ ያለበት የወላጅ/ሞግዚት መታወቂያ ምሣሌዎች፡-

- የመንጃ ፈቃድ
- ፓስፖርት
- የሞተር ተሽከርካሪ አስተዳደር (MVA) የመታወቂያ ካርድ
- ሌላ ህጋዊነት ያለው መታወቂያ

ከተማሪው(ዋ) ጋር ወላጅ/አሳዳጊ ስላላቸው ዝምድና-ግንኙነት ማረጋገጫ ምሳሌዎች፡-

- ስለ ወላጆች የሚገልጽ የተማሪ የልደት ሠርተፊኬት
- የፍርድ ቤት ትእዛዝ
- የመለያየት ስምምነት ወይም የፍቺ ድንጋጌ
- ሌላ ህጋዊ የሆነ መታወቂያ

## በደባልነት መኖሪያ ደጋፊ ሠነዶች

የሚቀርቡት የማረጋገጫ ማስረጃዎች በወላጅ/በሞግዚት/ብቁ ተማሪ በቅጹ የተሞላውን አድራሻ የሚያመለክት መሆን አለበት MCPS Form 335-74፣የደባልነት መኖሪያ ቤት ማረጋገጫ ቅጽ/Shared Housing Disclosure Form የላኪው ድርጅት ስም ያለበት፣ እና በ 90 ቀን ውስጥ የተላከ መሆን አለበት።

ስለ አድራሻ የሚገልጹ ተቀባይነት የሚኖራቸው ሠነዶች ከሚከተሉት ድርጅቶች መሆን አለበት፡-

- የገንዘብ ተቋማት (ማለት፡- ባንኮች፣ የመድን/የኢንሹራንስ ድርጅቶች፣ ወ.ዘ.ተ)
- የመገልገያ/ዩቲሊቲ ኩባንያዎች (ማለት፡- የስልክ፣ የውኃ፣ የማብራት-ኃይል፣ ወ.ዘ.ተ)
- መንግስታዊ (ማለት፡- ፌደራል፣ ስቴት፣ የአካባቢ)
- ህክምና
- የኃይማኖት ተቋማት
- አትራፊ ያልሆኑ/የማህበረሰብ ድርጅቶች

## ስልክ ቁጥሮች እና ድረ-ገጾች

- ካፒታል ፕላኒንግ ክፍል- Division of Capital Planning የስልክ ቁጥር፡- . . .240-314-4710
  www.montgomeryschools.org/departments/planning
- ዓለም አቀፍ ምዝገባ እና ምደባ International Admissions and Enrollment (IAE) የስልክ ቁጥር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . :- 240-740-4500
  www.montgomeryschoolsmd.org/info/enroll/
- የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የቤት አልባ ጉዳይ የሚከታተል MCPS Homeless Liaison የስልክ ቁጥር፡- . . . . . . . . . . . . . . . . . . .240-740-4511